# <u>ኢትዮጵያዊ የተባለው ጠበቃ ማነውሱ ?</u>
# <u>ሙያዊ ግዴታውንስ ያከበረና ሰብዓዊነትን</u>
# <u>የተላበሰ ነውን ?</u>

7-11-2011

አብዛኛዎቻችሁ ወገኖቻችን እንዲያው በደፈናው ይህን ጠበቃ ተብዬ ጥሩ አድርጋችሁ እንደምታውቁት አርግጠኞች ነን ።  የግለሰቡን ስም ከማስቀደም ይልቅ በተፈጸመው ኢ-ሰብዓዊ ጉዳይ ላይ አትኩረን ኅሊናዊ ፍርዳችሁን እንድትሰጡበት አንባብያንን በትኅትና እንጠይቃለን ።

በሀገራችን አንድ አባባል አለ " ሰው መሳይ በሸንጎ !!" ይባላል ።እኛ ለጥቃቱ ሰለባ የሆነች ልጅ ወላጆች ስንሆን ። እኛ ራሳችን በወያኔ ተገፍ ትረን ከሀገራችን የወጣንና ፤  በጀርመን ሀገር የምንኖር ጥገኞች ነን ። መቼም የሀገራችን ችግር ማለቂያ አጥቶ ፤  ስደቱ ለልጆቻችንም እንደ ታላቅ ገጸ-በረከት ቢደርስም ወላጆች ነንና ፤ ልጆቻችን የትም ሆኑ የት ልንጨነቅላቸውና ከሚደርስባቸው ችግር ነፃ ልናወጣቸው የወላጅነት ግዴታ እንደሚኖርብን ወላጆች ሁሉ ÷ ወይም ወደፊት የቤተሰብ ኃላፊ ነት ይኖርብናል የምትሉ ሁሉ የምትገነዘቡት ነው ።

ልጅቱ ሣምራዊት አበበ ትባላለች ፤  ከሀገሯ ይዘናት የወጣነው ገና ጨቅላ ኅፃን የ3 ዓመት ልጅ ሆና ነው ። ኢትዮጵያን አላደገችበትም አል ተማረችበትም ፤ የኖረችው በአብዛኛው ውጭ ሀገር ነው ። ትምህርቷን የጀመረችው በኬንያ ናይሮቢ ነበር ። ከዚያም ከመላው ቤተሰቦቿ ጋር ጀርመን መጥታ ትምህርቷን እስከ 10ኛ ክፍል ተምራለች ።

ስለዚህች ልጅም ሆነ ስለኛ የምንገልጸው ሁሉ ዕውነትና ፍጹም ዕው ነት ነው ።  የኛ ታሪክም ሆነ ማንነታችን በ UNHCR የታወቀና በግልጽ ተመዝግቦ ፤ በጀርመንም የታወቀና ውሸት ያልተደባለቀበት ነው ።

ይህች ልጅ በሰላም ከቤተሰቧ ጋር አብራ እያለች ፤ ትምህርቷንም እየተማረች በምትኖርበት ወቅት ፤ እኛ ወላጆች ሳንሰማና ሳናውቅ አንድ አሜሪካዊ ወታደር በስሙ Andros King የሚባል በጓደኝነት ይዟት በኋ ላም ግለሰቡ በንግግር ችሎታውና የሌለውን ሀብት እንዳለው በማስመሰል በሕጋዊ መንገድ አሜሪካ ይዟት ይገባል ።

አለኝ የሚለውም ሀብት ውሸት ሆኖ ተገኘ ። አሜሪካ ይዟት እንደገባ ወዲያው ጋብቻ ያድርጉ እንጂ መኖሪያሽን አሰጥሻለሁ ፤ የአሜሪካ ወታ ደር ስለሆንሁ ችግር የለብሽም ብሎ ያግባባት ሁሉ ውሸት ሆኖ ተገኘ ። እሷም ገና ከጀርመን ሳይወጡ ጸንሳ ስለነበረ የሷ ሴትነት ብቻ ሳይሆን የእርግዝና ደካማነቷን ተንተርሶ ምንም ልታደርገኝ አትችልም በሚል የወንድ ትምክህተኝነት !! በአንድ ቤት ውስጥ ወዲያ ወዲህ እንዳትላወስ አድርጎ ካቆያት በኋላ አንዲት ሴት ልጅ ወለደች ። ከዚያም ለስድስት ዓመታት ያለምንም መታወቂያ እንደፈለገው አቆያት ።  ይህ ከሰብዓዊ ግንዛቤና ርኅራኄ በፍጹም የራቀው አሜሪካዊ ወታደር ጭካኔው በሚስቱ ላይ ብቻ ሳይሆን ፤ ኅፃኗ ልጁ በተገቢው ጊዜ ትምህርት እንዳትጀምር ከእናቷ ጋር ቤት ተዘግቶባት እንድትኖር አድርጓታል ።

አሁን በመጨረሻው ይህች ታጋች ልጃችን በጣም ሲብስባት ፤" መብ ቴን አስከብርልኝ ፤ ወይም ለመንግሥት አመለክታለሁ ስትለው ፤ የፍ ቅር ማተቡን በጥሶ እርሷ ከርሱ የምትለይበትን ሁኔታ በመገፋፋት የብቸ ኝነት ሕይወቱን መረጠ ። በርግጥ እዚህ ላይ ግለሰቡ አንድ ሌላም ፍራቻ ነበረው ማለት ይቻላል ። ይኸውም ለመንግሥት ካመለከተች በፈጸመው ወንጀል ተጠያቂ መሆኑን በማመን ነበር ሊለያት የቆረጠው ። ልጅቱ ኅፃኗን ማለትም የ6 ዓመት ልጃቸውን ይዛ የፈለገችበት ብትሄድ ለሱ ደስ ታው እንደነበረ በመግለጹ ፤  ታጋችዋ ልጃችን እንደምንም አንድ ኢት ዮጵያዊ ወገን አግኝታ ፤ ባል ተብዬውን ትታው ኅፃን ልጇን ይዛ በሰው ቤት ጥገኝነት በሲያትል መኖር ጀመረች ።

ይህ ጉዳይ በዚህ መቀጠል አይገባውም ፤ ጉዳዩን ለሕግ ማቅረብ ያስ
ፈልጋል በሚል የወገን ምክር ፤ ነገሩን ከሕግ አዋቂ ተብዬው ጠበቃ ጋር
እንድትነጋገር ተደርጎ ነበር ። ጠበቃው የሷን ጉዳይ ጀምሮ ለመጨረስ
$8000/ ስምንት ሺህ ዶላር ይከፈለኝ ብሎ ይጠይቃል ። ይህች ልጅ
በምድረ አሜሪካ መታወቂያ የሌላት ፤ ከጎፃን ልጇ ጋር እየተንገላታች
ያለች በመሆኗ ያን ያህል ገንዘብ ልትከፍል አልቻለችም ። እኛም በስ
ደት እየተንገላታን በመሆናችን በአንድ ጊዜ መክፈል ባንችልም ከዘመድ
ተበድረንም ይሁን ወይም በወገን እርዳታ ግማሹን ገንዘብ ከፍለን ፤ ግማ
ሹን በመጨረሻ ልንከፍል ከጠበቃው ጋር በስልክ ተነጋግረን ተስማማን።
ጠበቃው ለኛ ቃል ሲገባልን "በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ መታወቂያዋንና
የሥራ ፈቃዷን አሰጣታለሁ ! የሷ ጉዳይ የበሰለ ነው ! ከአሜሪካዊው
የወለደች ስለሆነ የጋብቻ ወረቀትም ስላላት ምንም ችግር የለም ። የደረ
ሰባትን ችግር አንድ በአንድ ዘርዝራ ታቅርብልኝና ጉዳዩን ለኢሚግሬሽን
አቀርባለሁ ! " ስላለን የተባለውን $4086 / አራት ሺህ ሰማንያ ስድስት
ዶላር በባንክ ልከንለት ተቀብሏል ። እኛ በሱ አነጋገርና በኢትዮጵያዊነቱ
ልባችን ኮርቶ እምነታችን ጠንክሮ ፤ መቼም ወላጆች ነንና በልጅቱ ላይ
የተጋረጠው ችግሯ ይወገዳል ብለን መስማማታችን እሙን ነው ። ለዚህ
ለምንለው ሁሉ ብቃት ያላቸው ማስረጃዎቻችን በእጃችን ይገኛሉ ። በማ
ንኛውም ጊዜ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለፍርድ ቤትም የምናቀርበው ነው ።

## <u>አሁን በሣምራዊት ላይ ተደራራቢ ግፍ<br>እየፈጸመ ያለው ጠበቃ ማነውሱ? ለምን ?</u>

ኢትዮጵያዊያን ወገኖችና ለሰው ልጆች ሰብዓዊ መብት የቆማ
ችሁ ሁሉ ልብ በሉና ይህንን ጉድ አድምጡ ! ጠበቃው በአሜሪካ
በሚኖርበት ወቅት አንድ የራሱ የሆነ ገጸ-ባኅሪ እንዳለውና በዚህ
ተግባሩም ካሁን ቀደም በአንዲት እንስት ኢትዮጵያዊት ፈጽሟል
እየተባለ የሚናፈስለት ፤ እንዲያውም በአሜሪካ ጋዜጣ ላይ ወጥቶ
እንደነበረ የሚጠቁም ሁኔታ ከሰዎች የደረሰን ዕውነት ሆኖ መገኘ
ቱን በዚህ ላይ መግለጽ ፈልገን ሳይሆን ፤ ሁኔታው ግን ከሣምራዊት
ጋር የተያያዘ ሆኖ መገኘቱ በእጅጉ አስገርሞናል ። ይህ ከሙያው ግዴ
ታና ሕዝብን እንዲያገለግል ከተሰጠው የጥብቅና ፈቃድ ውጪ ከሰብዓዊ
ርኅራኄ የሸሸው ጠበቃ ተብዬ ፤ ይልቁንም እኛ ኢትዮጵያዊ ጠበቃ
በማግኘቷ ደስ ብሎን እሱ ለጠየቀው ገንዘብ ምንም ሳናቅማማ ከፍለ
ነው ገንዘቡን ከሣጥኑ ካስገባ በኋላ ፤ ያ መጥፎ ባኅሪው አገርሽቶበት ልጅ
ቱን ለስምንት ወራቶች ደጅ ከማስጠናቱ በላይ ፤ ለጓደኝነት ይጠይቃ
ትና ፈቃደኛ ሳትሆን በመቅረቷ " ካሁን በኋላ ያንቺ ጠበቃ አይደለሁም
" ብሎ ያለምንም ምክንያትና በራሱ ፈቃድ ጥብቅናውን አቋረጠባት ።
ሪዛይን አደረገ ። እኛ በዚህ ጉዳይ ግራ የተጋባነው ወላጆች በስልክ አነጋ
ግረነው ፤ የፈጸመው ድርጊት ለሕግም ሆነ ለሞራል ፍጹም ተፃራሪ በመ
ሆኑ ፤ ትክክል እንዳልሆነና የጀመረውን ጉዳይዋን ሊጨርስላት እንደ
ሚገባ ፤ ሌላው ቢቀር ስለ ኢትዮጵያዊነትህና ስለተሰጠህ የሥራ ፈቃድ
ስትል የገባኸውን ግዴታ ልትፈጽም ይገባሃል ብለን ብንገልጽለትም ፤ "
ኢትዮጵያዊነትን አላውቅም ይህ ቢዝነስ ነው ! የከፈላችሁትም $4086
ሥራውን ብሠራም ባልሠራም የኔ ገንዘብ ነው !! እንዲያውም ቀሪውን
ገንዘብ ትከፍሉኛላችሁ !! ይህን ጉዳይ ካሁን በኋላ አልሠራም ብሎ ፎከ
ረብን ። ለዚህ አባባሉም በቂ ማስረጃ በእጃችን ላይ ይገኛል ። ሌላ የተ
ለየ ተልዕኮ እንዳለው ባናውቅም ምናልባት ከሱ ርቀን ስለምንኖር በሕግ
ሊጠይቁኝ አይችሉም ፤ ወይም ስለ ሕግ ዕውቀቱ የላቸውም ብሎ በማሰ
ብም ሊሆን ይችላል !! ግን በጣም አሳዛኝ ግለሰብ ነው !! ያለመተዋወቃ
ችን እንጂ " እኔ የታገችዋ ወላጅ አባት በኢትዮጵያ በኖርሁበት ወቅት
እንኳንስ ለራሴ ጉዳይ ለሌሎች የምበቃ ፤ የኢትዮጵያን ሕግጋት ጠንቅቄ
የተማርሁ ፤ ሕጋዊ የጥብቅና ፈቃድም የነበረኝና ሀገሬን ባሉኝ የተለያዩ
ሙያዎች ሁሉ ያገለገልሁ ነኝ ።

ይህ ጠበቃ ተብዬው የፈጸመው ግፍ ታላቅ በመሆኑ ፤ ከዚህ ሥነ-ምግባር ከጎደለው አስተሳሰቡ እንዲቆጠብና የጀመረውን ሥራ እንዲፈጽም በሰዎች አስጠይቀነው ነበር ። ነገር ግን አጥጋቢ መልስ ባለመገኘቱ አስካሁንም ድረስ ለልጅቱ ምንም የተፈጸመላት ነገር ባለመኖሩ ልጅቱ ከ'ነፃኗ ጋር በጭለማ ሕይወት ውስጥ ትገኛለች ። ይህን ጉዳይ ሰብዓዊ ኅሊና ያለው ሁሉ ይፈርደዋልና ለአደባባይ ልናበቃው ግድ ሆኖብናል ።

በመሠረቱ አሜሪካ የወንጀለኞች ዋሻ ሳትሆን ፤ የግለሰቦች ነፃነት የተከበረባት ሀገር መሆኗን በታሪክ እናውቃለን ። በተግባርም እየታየ መሆኑን ዓለም ያውቀዋል ። እንዲያውም አንድ ወቅት አንድ ግለሰሰብ የእስልምና ሃይማማኖትን ቅዱስ ቁርዓን አቃጥላለሁ ብሎ ሲዝት ፤ የአሜሪላው ፕሬዚዳንት ኦባማ ያሉትን ብጠቅስ የአሜሪካንን የሰብዓዊ መብት ጠባቂነት መገንዘብ አያዳግትም ። ኦባማ ምን አሉ ? '' ይህ አሜሪካ ነው የዘር ወይም የሃይማኖት ልዩነት የሚካሄድበት ሀገር ስላልሆነ ፤ መጽሐፍ ልታቃጥል አይገባህም ! '' ነው ያሉት ። ይህ ጠበቃ ተብዬው ግን የሰው መሣይ በሸንጎ ካባውን ለብሶ ! በጥብቅናው ያገኘውን ዝና ተንተርሶ ! የራሱ ወገን በሆነች ኢትዮጵያዊት ሴት ልጅ ላይ ፤ ለዚያውም የጠየቀው ገንዘብ ተከፍሎት እያለ ፤ ለጊዜያዊ ወሲብ ጥያቄ ሲል የጥብቅና ግዴታውን ረጋግጦ ፤ በተከበረች አሜሪካ ይህን ቅሌት በማሳየቱ ከልባችን ማዘናችንን ለወገኖቻችን ሁሉ እንገልፃለን ። ተጠቃሹ ጠበቃ እንኳንስ የጠየቀው ገንዘብ ተከፍሎት ይቅርና በዚህ መከራ ዘመን መከራ ውስጥ ለገቡ ወገኖቹ ሊቆም በተገባው ነበር !! ዳሩ ግን አንዳች ፋይዳ ሳያደርግ እየሠራሁ ያለሁት ቢዝነስ ነው ብሎ ገንዘባችንን በግፍ በልቶ ካደን !! በመሠረቱ በተግባር እንጂ ባለዝና በመሆን ብቻ ከጥብቅና ፈቃድ ውጭ ዘረፋ የሚከውኑበት የጥብቅና ፈቃድ በየትም ዓለም እንደሌለ ጠበቃው ማወቅ ይገባው ነበር ! ግን ይህ ያለምንም በቂ ምክንያት የተፈጸመው ቅሚያ-ዝርፊያ የሱን ማንነት ጉልህ አድርጎ በማሳየቱ ፤ የልጅቱንም ኬዝ በማበላሸቱ ከሰውም ይሁን ከፈጣሪው ፍርዱ አይቀሬ ነው !!

የሣምራዊት መከራና ሥቃይ እንዲህ ተነግሮ የሚያልቅ አይደለም ። እሷ ከደረሰባት መከራ የተነሳ በጭንቀትና በህመም እየተጎዳች ነው ። በዚያ ላይ ከ'ነፃን ልጇ ጋር ያለረዳት እየኖረች ነው ። ባጠቃላይ የደረሰባት ፈተና ተፈጥሮን የሚያስጠላ በመሆኑ ችግሯን በዚህ ላይ አውስተን ልንጨርሰው የማይቻል ነውና የገለጽነው ጥቂቱን ነው ።

1/ ሚስት አድርጎ የወሰዳት ወታደር ውሸታም ሆኖ ተገኘ ! 2/ ጠበቃው ለአገልግሎቱ እንዲከፈለው የጠየቀውን ገንዘባችንን በበንክ ከፍለነው በልቶና የገባውን ቃል ክዶ ፍትሕን ረጋግጦ ተገኘ ። 3/ ከሶስት ገጽ ባልበለጠ ደብዳቤ ለዚያውም ልጃችን ጽፋ የሰጠችውን ለኢሚግሬሽን ልኮላት ፤ ኢሜግሬሽንም አሻራና የጋብቻ ወረቀት ፤ እንዲሁም የባለቤቷን የዜግነት ወረቀት እንዲያቀርብ ጠበቃው ተጠይቆ ነበር ፤ ነገር ግን ከሙያው ይልቅ የተመኘውን ሴትን ልጅ የመዳፈር ፍላጎቱ ስላየለበት !! ልጅቱም የጠየቀውን አላደርገውም በማለቷ ኬዝዋን በማበላሸት ክህደት ውስጥ ገባ ። 4/ $4086 ዶላር ወስዶ ብሠራም ባልሠራም የተከፈለው ገንዘብ የኔ ገንዘብ ነው ብሎ በመፎከርና በመዛት ካሁን በኋላ ጠበቃሽ አይደለሁም ሲል ሪዛይን አደረገ ። ለመሆኑ የተከፈለው ገንዘብ የሱ ገንዘብ የሚሆነው በምን ምክንያትና በየትኛው ሕግ ነው ? እንዲህ ዓይነቱ ድርጊትስ በየትኛው ሀገረ-መንግሥት ተፈጽሞ ያውቃል ? ድርጊቱስ መንገድ ላይ ቆመው የሕዝብን ሀብት ከሚነጥቁ ዘራፊዎች በምን ይለያል ? ይህ ድርጊት በቅንነት ሥራቸውን እየሠሩ ሕዝባቸውን የሚያገለግሉ ጠበቆችን አያሰወቅስምን ? ይህ ከጠበቆችና ከማንኛውም ምሁር ውጭ በዚህ መጥፎ ሥነ-ምግባር የተዘፈቀው ግለሰብ በምን ምክንያት ይሆን ይህን መሰል ግፍ በራሱ ወገን ላይ ለፈጽም የበቃው ብለን ብንጠይቅ መልሱ ምን ይሆን ? የዚህን ታሪካዊና ዓይን ያወጣ ወንጀል የተመለከታችሁ ያደመጣችሁ ለሰብዓዊ ጉዳይ የቆማችሁ ኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳትሆኑ የዓለማት ማኅበረ-ሰብ ሁሉ ይፈርዱን ዘንድ መግለጽ ግድ ስለሆነብን አቅርበነዋል ። በም

ትሰጡን ኅሊናዊ ፍርድ ብቻ ሳይሆን ፤ ጉዳዩ በቀረበበት ሜዲያ ሁሉ የመሰላችሁን ኅሊናዊ አስተያየት በመስጠት ፤ ኢትዮጵያዊት ወገናችሁን ከደረሰሰባት ችግር ታላቅቋት ዘንድ እንማጸናለን ፡፡ ይህ ግለሰብ ችግር ያደረሰው በኛ ላይ ብቻ ሳይሆን ፤ ተመሳሳይ ችግር በሌሎችም ላይ ያደረሰ መሆኑን ከተለያዩ አቅጣጫዎች ስለሰማን ፤ የማንኛችሁም አስተያየት አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይደለም ፡፡ ምክንያቱም ይህንን ሕገ-ወጥ ግለሰብ የፈለገውን ያድርግ ብሎ ጥቃትን በዝምታ ማለፍ ተገቢ ባለመሆኑና ፤ ግለሰቡን ያላወቁ ሌሎች ወገኖቻችን የጥቃቱ ሰለባ እንዳይሆኑ ለመከላከል ሲባል ነው ፡፡ ካሁን ቀደም ጥቃቱ የደረሰባቸውና በፍርሃት ቆፈን ተይዘው ግለሰቡ ማንም የማይደፍረው አንበሳ እስኪሆን መጠበቅ ማለት ከወንጀል ተባባሪነት ልዩነት ስለማይኖረው ማጋለጡ ግን ለወገኖቻችን ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለን እናምናለን ፡፡ የጠበቃውን ስም ማወቅ አስፈላጊ በመሆኑም ዶክተር ሼክስፒር ፈይሣ ይባላልና ዕወቁት፡፡

ስለዚህ ይህ ጉዳይ የሚመለከታችሁ የመንግሥት መ/ቤት ኃላፊዎችና የሴቶች መብት ተከራካሪዎች ፤ የሰብዓዊ መብት ጠባቂ ድርጅቶች የበኩላችሁን ሕጋዊ እርምጃ በመውሰድ ለተጠቃሹ ጠበቃ ፍትሕ ምን እንደ ሆነ በማሳየት የታጋችዋንና ፍትሕ ያጣችው ልጃችንን ከኅፃን ልጅዋ ጋር መብቷእንዲበርላት ታደርጉልን ዘንድ በትኅትና እንጠይቃለን ፡፡ ለሚደረግልን ትብብር ሁሉ የላቀ ምሥጋናችንን አስቀድመን እናቀርባለን ፡፡

ከአክብሮት ጋር

እናቷ ወ/ሮ በልዩ ስለሺ

አባቷ አቶ አበበ አረዳ

ግልባጭ ፡- ለአሜሪካ ኮንሱላር ጀርመን

: ለአሜሪካ ኢሚግሬሽን መ/ቤት ሲያትል

: ለጀርመን ቡንደስ አምት

: ለኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ ሴቶች ሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች